የኢትዮጵያ ፌዴራላ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAAL NEGARIT GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ-ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ ሺ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 28
ADDIS ABABA- 24th April, 2008

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፶/፪ሺ
የናዝሬት ሸራና ልብስ ስፌት ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፬ሺ፷፭

## CONTENTS

*Regulation No 150/2008*
Nazareth Canvas Sewing and Garment Factory Establishment Council of Ministers Regulation Page...4065

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶/፪ሺ

### <u>የናዝሬት ሸራና ልብስ ስፌት ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ::

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የናዝሬት ሸራና ልብስ ስፌት ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶/ ፪ሺ. ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል ::

፪. <u>መቋቋም</u>

፩) የናዝሬት ሸራና ልብስ ስፌት ፋብሪካ (ከዚህ በኋላ ‹‹ድርጅት›› እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪) ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ::

*Council of Ministers Regulation No 150./2008*

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF NAZARETH CANVAS SEWING AND GARMENT FACTORY*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *SHORT TITLE*

   This Regulation may be cited as the "Nazareth Canvas Sewing and Garment Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 150./2008."

2. *ESTABLISHMENT*

   1) Nazareth Canvas Sewing and Garment Factory (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

   2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

ያንዱ ዋጋ
Unite Price 2.30

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negarit Gazeta P.O. Box 2445

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል ::

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዳማ ከተማ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ሊኖረው ይችላል ::

፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

፩) የመከላከያን ሠራዊት የትጥቅ ፍላጐት ለማሟላት ወታደራዊ የደንብ ልብሶችን ፣ የሸራ ፣ የቆዳ ፣ የጥብጣብ ውጤቶችን እንዲሁም የማዕረግ ምልክቶችን አምርቶ ማቅረብ ፤
፪) በተጓዳኝ የተለያዩ የሲቪል አልባሳትንና የሸራ ውጤቶችን አምርቶ ለገበያ ማቅረብ እና
፫) ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ በሚረዳ በማናቸውም ሌላ የንግድ ሥራ መሰማራት

፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩፻ ሚሊዮን (ብር አንድ መቶ ሚሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፵ ሚሊዮን ፱፻፹፮ሺ፯፻፳፫ ከ፶፪ ሳንቲም (አርባ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ሦስት ብር ከሃምሣ ሁለት ሣንቲም) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል ::

፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ::

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ::

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Supervising Authority*

The Ministry of National Defense shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Adama town, and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to manufacture and supply as per the army requirement military uniforms, canvas, leather, and stripes made articles and insignias;
2) in parallel to manufacture and sell different civilian articles and canvas made articles; and
3) to engage generally in any other business conductive to the attainment of its purpose.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 100,000,000.00 (One Hundred Million Birr) of which Birr 40,986,723.52 (Forty Million Nine Hundred Eighty Six Thousand Seven Hundred Twenty Three Birr and Fifty Two Cents) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall note be liable beyond its total assets

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of April, 2008

*MELES ZENAWI*
*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*